ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህንድ የሀሳብ ጉባኤ ላይ ዋና ዋና ሀሳቦችን አቀረቡ።

ሐምሌ 15/2012 ዓ.ም

አለም አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ሊገኝ የሚችለው በጠንካራ የሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ ብቃት ነው፡ የህንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር በ‹አትማኒርባር ባራት› ጥሪ መሰረት የበለፀገ እና እድገት ያለው አለም ለመፍጠር አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ

በህንድ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ከዚህ የተሻለ ጊዜ ፈጽሞ የለም፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ

ህንድ የአማራጮች ሀገር ሆና መጥታለች፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ

የህንድ-ዩኤስ አጋርነት አለም ከወረርሽኙ በኋላ በፈጣን ሁኔታ ለማደግ እንዲችል በመርዳት ጠቃሚ ሚና ይጫወታል፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ሽሪ ናሬንድራ ሞዲ ዛሬ በተካሄደው የህንድ የሀሳቦች ጉባኤ ላይ ጠቃሚ ነጥቦችን አንስተዋል። ጉባኤው በዩኤስ-ህንድ ቢዝነስ ካውንስል (ዩኤስአይቢሲ) ተዘጋጅቷል። የዚህ አመት ጉባኤ መሪ ቃል ‹የተሻለ ነገን መገንባት› የሚል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አመት 45 ኛ የዩኤስአይቢሲ ተሳታፊዎችን እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የህንድ-ዩኤስ የኢኮኖሚ አጋርነቱን የላቀ ስራ እንዲያከናውን የዩአይቢሲ አመራር ቁርጠኝነትን አመስግነዋል።

ጠንካራ የሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ ብቃትን በማሳደግ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእድገት ዋና መሰረታዊ አጀንዳ ላይ ድሆችን እና ተጋላጮች ላይ ስለ መስራት አስፈላጊነት ተናግረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹ህይወትን ማቅለል› እንደ ‹ቢዝነስን ማቅለል› በተመሳሳይ ሁኔታ ጠቃሚ መሆኑን አስምረውበታል። እርሳቸው እንዳሉት ይህ ወረርሽኝ የውጪ ስጋቶችን ለመከላከል ጠንካራ አለም አቀፍ ኢኮኖሚ የመመስረት አስፈላጊነትን በማውሳት ጠንካራ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ብቃትን ማሳደግ እንደሚቻል ገልፀዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በትኩረት እንደተናገሩት ህንድ የ‹አትማኒርባር ባራት› ጥሪን ግልጽ በማድረግ የበለፀገ እና ያደገ አለምን ስለሚፈጠርበት ሁኔታ አስተዋጽኦ እያደረገች መሆኑን ተናግረዋል።

ህንድ የተቀናጀ ትክክለኛ አቃፊነት፣ እድል እና አማራጮችን አቅርባለች።

ኢኮኖሚያችንን የበለጠ ክፍት እና በለውጥ የተቃኘ ለማድረግ ለውጦች ተወዳዳሪነት እንዲፈጠር ግልጽነት እንዲኖር፣ ዲጂታይዜሽን በማስፋፋት የበለጠ ፈጠራ እና የበለጠ የፖሊሲ መረጋጋት እንዲኖር ያስችላል።

የቅርቡን ሪፖርት በመጥቀስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት ከከተማ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ይልቅ የገጠር የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር ይበልጣል። ህንድን እንደ እድል ሀገር ያሞካሹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ግማሽ ቢሊየን ገደማ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን ከግማሽ ቢሊየን በላይ ሰዎች ከኢንተርኔት ጋር የተገናኙ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀዳሚ ቴክኖሎጂዎች እድል 5 ጂ፣ ትልቅ ዳታ አናሊቲክስ፣ ኳንተም ኮምፒዩቲንግ፣ ብሎክ- ቼን እና ኢንተርኔት ኦፍ ቲንግስ ጠቅሰዋል።

በዘርፎች ላይ ኢንቨስት የማድረግ ትልቅ እድል

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስመሩበት በህንድ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት የማድረግ ትልቅ እድል አለ። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርብ የተካሄደው ታሪካዊ ለውጥ በእርሻ ዘርፍ ላይ በእነዚህ ዘርፎች የእርሻ ግብዓት እናማሽነሪ፣ የእርሻ አቅርቦት ሰንሰለት፣ የምግብ ማቀነባበሪያ ዘርፍ፣ የአሳ ምርት እና ኦርጋኒክ አሰራር ላይ ኢንቨስት የማድረግ እድል አለ ብለዋል። የጤናው ዘርፍ በህንድ በየአመቱ በ 22% ፈጣን እድገት እያስመዘገበ ሲሆን የህንድ ኩባንያዎች በህክምና-ቴክኖሎጂ ምርት፣ ቴሌ-ህክምና እና ምርመራ እያደገ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በህንድ የጤና ክብካቤ ዘርፍ ለማስፋፋት ኢንቨስት ለማድረግ የተሻለው ጊዜ ነው ብሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌሎች በርካታ ዘርፎች ኢንቨስት ለማድረግ በርካታ እድል የሚያቀርቡ የሐይል ዘርፍ፣ የመሰረተ ልማት ፈጠራ ቤቶችን መገንባ፣ መንገዶች፣ አውራ መንገዶች እና ወደቦች፣ ሲቪል አቬሽን፣ ጨምሮ ትላልቅ የህንድ የግል አየር መንገዶች ከሺዎች በላይ አዳዲስ አውሮፕላኖችን በሚቀጥለው አስር አመት ጊዜ ውስጥ ለመሰማራት አቅደዋል። ስለሆነም ለማንኛውም ኢንቨስተር በህንድ የአምራች አገልግሎቱን ለማስፋፋት እድል የሚከፍት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የጥገና እና እድሳት እንዲሁም የኦፕሬሽን አገልግሎት በኩል እድል ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህንድ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” በመከላከያው ዘርፍ ወደ 74% ያሳደገች ሲሆን ሁለት የመከላከያ ኮሊደሮች የመከላከያ መሳሪያዎችን እና አቅርቦቶችን ምርት ለማበረታታት የተቋቋሙ ሲሆን ልዩ ማበረታቻ ለግሉ ዘርፍ እና ለውጭ ኢንቨስተሮች እንደሚደረግ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህዋ ዘርፍ ላይ ወሳኝ ለውጥ እየተደረገ ነው ብሏል።

በፋይናንስ እና በኢንሹራንስ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህንድ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ጣሪያ ለኢንቨስትመንት ኢንሹራንስ ወደ 49% ያሳደገች ሲሆን 100% የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) በኢንሹራንስ ስራዎች እንዲሳተፍ ተፈቅዶለታል። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጤናው ዘርፍ፣ እርሻ፣ ንግድ እና የሕይወት ኢንሹራንስ ሽፋኑን ለማሳደግ ትልቅ ያልተነካ እድል እንዳለ ጠቁመዋል።

ኢንቨስትመንትን በህንድ ማሳደግ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ህንድ የአለም ባንክ የንግድ ደረጃ ማደግ ተናግረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት በየአመቱ ህንድ “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” ከፍተኛ እድገት ላይ የደረሰች ሲሆን “የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት” የውስጥ ፍሰት በህንድ በ 2019-20 ሰባ አራት ቢሊየን ዶላር ሲሆን ከአለፈው አመት በ 20% ጭማሪ አሳይቷል።

በህንድ ኢንቨስት ለማድረግ ተመራጩ ጊዜ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት ከህንድ የአለም አቀፍ የኢኮኖሚ የማገገም አስፈላጊው ሀይል አላት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት የህንድ ማደግ በንግድ እድሎች ማደግ ማነስ ሲሆን ሀገሪቱ እምነት የሚጣልባት ለማድረግ አለም አቀፍ ውህደት አቃፊነትን በማሳደግ በገበያ ተወዳዳሪነት እንዲሁም ህንድ በተፈጥሮአዊ አጋርነት አለም ከወረርሽኙ በኋላ በፍጥነት እንዲያድግ ጠቃሚ ሚና መጫወት ትችላለች ብሏል። ጠቅላይ ሚኒስተሩ ለአሜሪካ ኢንቨስተሮች እንደተናገሩ በህንድ ኢንቨስት የማድረጊያው ጊዜ አሁን ነው ብሏል።

ኒው ደልሂ

ሐምሌ 15/2012 ዓ.ም